# ሥነ-ጥበባት

## የተማሪ መፅሐፍ

## አንደኛ ክፍል


**አፋን ኦሮሞ አዘጋጆች**

ደንደኣ ቦጋለ

ደሜ ቶሊና

ታደሰ ድንቁ

**አፋን ኦሮሞ ኤዲተሮች**

ከበቡሽ ለሜሳ

ለሚ ቤኛ

ሉባባ ጀማል

**በአፋን ኦሮሞ ገምጋሚዎች**

ድርባ ማሞ

ደቀቦ ጉዬ

እስማኤል ሐሰን

**ተርጓሚ**

ይልፋሸዋ ጥላሁን

**ኤዲተር**

ደቀቦ ጉዬ

**ግራፊክስ**

ታደሰ ድንቁ

**ገላጭ ስዕል**

ብዙአየሁ ግርማ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2014/2022

ይህ መጽሐፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በአሰላ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ትብብር በ2014/2022 ተዘጋጀ፡፡

የዚህ መጽሐፍ የባለቤትነት መብት በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፈቃድ ውጪ በሙሉም ሆነ በከፊል ማሳተምም ሆነ አባዝቶ ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል፡፡

ማውጫ


ምዕራፍ 1 የስነ ጥበብ ግንዛቤ ..... 1

1. ምልከታ ..... 1

1.1. የስዕሎች መልእክት ..... 1

1.2 መዝሙር ማዳመጥና ማየት ..... 9

1.3 ምስለ ድምፅ ማየትና ማዳመጥ ..... 17

ምእራፍ 2 የፈጠራ ችሎታ ..... 24

2.1 አድናቆትን መግለፅ ..... 25

2.2 መስመሮችን በተለያየ አቅጣጫ በማስመር ማቅለም ..... 29

2.3 የቤተሰብ መዝሙር ..... 37

2.4. መዝሙርና ጭፈራ በቀላል ምት ..... 42

ምዕራፍ 3 የታሪክና የባህል ተጨባጭ ሁኔታ ..... 44

3.1 የአካባቢና የህብረተሰብ ሙያዎች ..... 44

3.2. የአካባቢ ቀለማት ..... 63

ምእራፍ 4 የስነጥበባትማራኪነት ..... 68

4. አስደናቂ የባህል ክንውን ..... 68

4.1. የቤተሰብ መዝሙርና ውዝዋዜ ..... 68

4.2. የቤተሰብን የስራ ድርሻ በድራማ መልክ መግለጽ፡፡ ..... 70

4.3 የቤተሰብ ስዕል ..... 74

ምእራፍ 5 የስነጥበባት ግንኙነት ..... 78

5.1. በቡድን በመዘመር የራስን ተፈጥሯዊ ድምፅ ማሳደግ ..... 78

5.2. የታሪካዊ ቦታዎች ግንኙነትና ትግበራ ..... 84

# ምዕራፍ 1
# የስነ ጥበብ ግንዛቤ

## 1. ምልከታ

### 1.1. የስዕሎች መልዕክት

#### 1.1.የቤተሰብ ስዕል

**የግንዛቤ ጥያቄዎች**

1. ከዚህ በታች ያለው ስዕል ስንት የቤተሰብ አባላት አለው?
2. ከዚህ በታች ባለው ስዕል ውስጥ የሚታዩ ነገሮች ምን ምን ናቸው?



ቤተሰብና ግቢያቸው

## የግንዛቤ ጥያቄዎች

1. ከዚህ በታች በስዕል ከተዘረዘሩት ጨዋታዎች ውስጥ የትኛውን ተጫውታችሁ ታውቃላችሁ ?
2. በአካባቢያችሁ ምን አይነት ጨዋታዎችን ትጫወታላችሁ?



የሰኞ ማክሰኞ ጨዋታ



የገመድ ጉተታ ጨዋታ



የገመድ ዝላይ ጨዋታ



እጅ ለእጅ በመያያዝ ክብ የመስራት ጨዋታ





የትምህርት ቤት ውስጥ ጨዋታዎች



ህፃናት የመምህራቸውን ምክር ሲያዳምጡ

### 1.1.2. የትምህርት ቤት ስዕል

**የግንዛቤ ጥያቄዎች**

1. የትምህርት ቤታችሁ ስም ምን ይባላል?
2. በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ምን ምን ይገኛል?





ልጆች በትምህርት ቤታቸው ቅጥር ግቢ ውስጥ የተለያዩ ጨዋታዎች ሲጫወቱ

## 1.1.3. የትራፊክ እንቅስቃሴ

### የግንዛቤ ጥያቄዎች

1. የመኪና መንገድ እንዴት ታቋርጣላችሁ?
2. በሚቀጥለው ስዕል ውስጥ የመኪና መንገድ እንዴትና በየት በኩል ማቋረጥ እንዳለባችሁ አመልክቱ፡፡



ህፃናት የመኪና መንገድ ሲያቋርጡ





ልጆች የመኪና መንገድ ሲያቋርጡ





ልጆች ወንዝ ሲሻገሩ

## 1.2 መዝሙር ማደመጥ፣ ማየትና መዘመር

### የግንዛቤ ጥያቄ 1

1. መዝሙር ትወዳላችሁ?
2. ምን አይነት መዝሙር ዘምራችሁ ታውቃላችሁ?



## የልጆች ጨዋታ መዝሙር 1

ማንበብ እወዳለሁ
ሁልግዜ አነባለሁ
ባነበብኩኝ ቁጥር
ይገባኛል ሚስጥር፡፡
ሚስጥር ሚስጥር/×2
የእውቀትን ሚስጥር
እኔ ልንገራችሁ
ከየ መፅሀፍ
ታገኙታላችሁ፡፡
ሚስጥር ሚስጥር/×2

## የልጆች ጨዋታ መዝሙር 2



ፀሐይ ፈነጠቀች
ብርሃንዋን አበራች
ኑ ልጆች እንጫወት
ፀሐይ ፀሐይ ወጣች /×2

ብርሃንዋን እያሳየች
ጨለማን አባረረች
ኑ ልጆች እንጫወት
ፀሐይዋ ሳትጠልቅ/×2
ፀሐይዋ ፀሐይዋ ወጣች/×2



## የልጆች ጨዋታ መዝሙር 3

## ትምህርት ቤቴ



…ትምህርት ቤቴ

ያደኩብሽ
የተማርኩብሽ
ኑሪ ለዘላለም
እንደኮራሁብሽ 2x

ትምህርት ቤቴ
የእውቀት ገበታዬ
አንቺ ስለሆንሽ
የምታሳድጊኝ
በእውቀት ኮትኩተሽ
ዛሬም ነገም ሁሌም እኔ ወድሻለሁ
እድገትና ልማት እመኝልሻለሁ፡፡

አስተማሪዎቼ ይግባችሁ ምስጋና
እውቀት የምቀስመው ከናንተ ነውና
ዛሬም ደጋግሜ አመሰግናለሁ
ሀ ለ መ ሰ ብዬ መቁጠርን ችያለሁ×2

## የልጆች ጨዋታ መዝሙር 4

### የአማርኛ ቋንቋ ፊደላት መዝሙር

## የግንዛቤ ጥያቄ

1. የአማርኛ ቋንቋ ፊደላትን በመዝሙር ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
2. ከዚህ በፊት የተማራችሁን በማስታወስ ከዚህ በታች የተሰጡትን የአማርኛ ቋንቋ ፊደላት በቅደም ተከተል ዘምሩ፡፡

## የአማርኛ ቋንቋ ፊደላት

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ለ | መ | ሰ | ረ | ሸ | ቀ | በ | ተ | ቸ | ነ | ኘ |
| አ | ከ | ወ | ዘ | ዠ | ገ | ደ | ጀ | የ | ጠ | ጨ | |
| ፀ | ጸ | ፈ | ፐ | | | | | | | | |

### የአማርኛ ቋንቋ ፊደላት

| | | |
|---|---|---|
| 1. ሀ ha | 12. ቸ che | 23. የ ye |
| 2. ለ le | 13. ኀ kHa | 24. ደ de |
| 3. ሐ Ha | 14. ነ ne | 25. ጀ je |
| 4. መ me | 15. ኘ ñe | 26. ገ ge |
| 5. ሠ se | 16. አ A | 27. ጠ Te |
| 6. ረ re | 17. ከ ke | 28. ጨ Che |
| 7. ሰ se | 18. ኸ He | 29. ጰ P'e |
| 8. ሸ she | 19. ወ we | 30. ጸ Ts'e |
| 9. ቀ qe | 20. ዐ 'a | 31. ፀ Tz'e |
| 10. በ be | 21. ዘ ze | 32. ፈ fe |
| 11. ተ te | 22. ዠ zhe | 33. ፐ p'e |



## ተግባር

የሚከተለውን ስለ አማርኛ ቋንቋ ፊደላት በምስል-ድምፅ የተዘጋጀውን በማዳመጥና በማየት ወይም በመምህራችሁ መሪነት በመደጋገም ከተለማመዳችሁ በኋላ በቡድን ዘምሩ፡፡

### የአማርኛ ቋንቋ ፊደላት መዝሙር

| | |
|---|---|
| ሀ ለ መ | ብዬ መቁጠር ጀመርኩ |
| ሰ ረ ሸ | በማለት አስከተልኩ |
| ቀ በ ተ | የፊደል አካላት |
| ቸ ነ ኘ | የመሀል ፊደላት |
| አ ከ ወ | ብዬ ቀጥላለሁ |
| ዘ ዠ ገ ን | ደሞ አስከትላለሁ |

ደ ጀ የ ለማለት አልደክምም
ጠ ጨ ፀ ን ሳልቆጥር አላልፍም
ጰ ፊ ፐ ብዬ አሳርጋለሁ
ፊደላትን ሁሉ እዚህ እማራለሁ፡፡/ 3

## የልጆች ጨዋታ መዝሙር 5

### የሚያማምሩ ሙዞች

| የግንዛቤ ጥያቄ |
|---|
| ምን እንቆጥራለን ? |




አምስት የሚያማምሩ ሙዞች አሉኝ
አንዱን ስበላ አራት ይቀራሉ
አራት የሚያማምሩ ሙዞች አሉኝ




አንዱን ስበላ ሶስት ይቀራሉ

ሶስት የሚያማምሩ ሙዞች አሉኝ




አንዱን ስበላ ሁለት ይቀራሉ
ሁለት የሚያማምሩ ሙዞች አሉኝ




አንዱን ስበላ አንድ ይቀራሉ
አንድ የሚያምር ሙዝ አለኝ




እሱን ስበላ ምንም አይቀርም/ ×3

## 1.3 መዝሙር ማዳመጥና መዘመር



ህፃናት መዝሙር በማዳመጥ በደስታ ሲጨፍሩ

ደስተኛ የሆነ
ደስተኛ የሆነ
ይጫወት



ደስተኛ የሆነ ያጨብጭብ
ቸብ ችብ
ድስተኛ የሆነ ደስታውን ለመግለፅ
ደስተኛ የሆነ ያጨብጭብ
ችብ ቸብ
ደስተኛ የሆነ ይደንስ
ዳንስ ዳንስ
ድስተኛ የሆነ ደስታውን ለመግለፅ
ደስተኛ የሆነ ይደንስ
ዳንስ ዳንስ
ደስተኛ የሆነ በጣም ይሳቅ
ሀ ሀ ሀ
ድስተኛ የሆነ ደስታውን ለመግለፅ
ደስተኛ የሆነ በጣም ይሳቅ
ሀ ሀ ሀ
ደስተኛ የሆነ ወደላይ ይዝለል
ዘለል ዘለል
ድስተኛ የሆነ ደስታውን ለመግለፅ
ደስተኛ የሆነ ወደ ላይ ይዝለል
ዘለል ዘለል
ደስተኛ የሆነ ይዘምር
ሻላላ
ድስተኛ የሆነ ደስታውን ለመግለፅ
ደስተኛ የሆነ ይዘምር

## ሻላላ

ድስተኛ የሆነ ሁሉን ይበል
ቸብ ቸብ ዳንስ ዳንስ ሻላላ
ደስተኛ የሆነ ደስታውን ለመግለፅ
ደስተኛ የሆነ ሁሉን ይበል
ቸብ ጭብ ዳንስ ዳንስ ሻላላ

### ተግባር 1

ስለ እነዚህ ስዕሎች የተዘጋጀውን መዝሙር ካዳመጣችሁ በኋላ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተጫወቱ፡፡



## የቤተሰብ አበላት መዝሙር

የቤተሰብ አባላት መዝሙር ፡ ከዚህ በታች ያለውን መዝሙር በሁለት ቡድን ተከፍላችሁ በመቀባበል ዘምሩ።

| ቡድን አንድ | ቡድን ሁለት |
|---|---|
| እናትና አባቴን | እወዳለሁ |
| ወንድምና እህቴን | እወዳለሁ |
| በሰላምና በፍቅር | እኖራለሁ |
| **ቡድን አንድ** | **ቡድን ሁለት** |
| ቤተሰቦቼ | ያሳድጉኛል |
| ቤተሰቦቼ | ይንከባከቡኛል |
| ቤተሰቦቼ | ያስተምሩኛል |
| **ቡድን አንድ** | **ቡድን ሁለት** |
| የእናትህ እናት ምንህ ናት ? | ሴት አያቴ |
| ያባትህ አባት ምንህ ነው? | ወንድ አያቴ |
| **ቡድን አንድ** | **ቡድን ሁለት** |
| አጎት ማነው? | ያባት የእናት ወንድም |
| አክስት ማናት? | ያባት የእናት እህት |
| **ቡድን አንድ** | **ቡድን ሁለት** |
| እንዚህ ሁሉ | ቤተሰባችን |
| እንወዳቸዋለን | እንደራሳችን |

## ተግባር 2

1. ከዚህ መዝሙር ምን ተረዳችሁ? ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡
2. የቤተሰቦቻችሁን አበላት ለጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡



### “የቀዩ ጫማ ምስለ-ድምፅ”

መምህራችሁ ይህንን ምስለ-ድምፅ ከሳዩዋችሁ በኋላ ካያችሁትና ከሳማችሁት ምን እንደተማራችሁ ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡



ደራርቱ የአያቷን ምክር አልሰማ ብላ ቀዩን ጫማ አድርጋ እየሮጠች ነው፡፡





ቀዩ ጫማ ደራርቱን ይዞ ጫካ ውስጥ አስገባት፡፡

## መልመጃ 1

1. ደራርቱ የአያቷን ምክር ያለመስማትዋ ለምን ችግር አጋለጣት?
2.
3.
4.
5.

# ምዕራፍ 2
# የፈጠራ ችሎታ

## ስሜትን መግለፅ

### ሰማይ መሬትና ውሀ





## 2.1. የቤተሰብ ሚናን ማስመሰል

**መልመጃ 1**

1. ቤተሰቦቻችሁ በቤት ውስጥ ምን ምን እንደሚሰሩ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡















የቤተሰብ አባላት የተለያዩ ስራዎችን ሲሰሩ

## 2.1.1. የራስን ቤተሰብ አለባበስና አነጋገር ማስመሰል



የእናቶች አለባበስ ማስመሰል

**መልመጃ 2**

1. የእናታችሁን ልብስ ለብሳችሁ ታውቃላችሁ?

## 2.1.2. የአባቶች አለባበስ

**መልመጃ 3**

1. አባታችሁ ምን አይነት ልብስ ይወዳሉ?



**መልመጃ 4.**

የቤተሰቦቻችሁን አለባበስ፣ አካሄድና አነጋገር በማስመሰል ለጓደኞቻችሁ አሳዩ!

## 2.2. መስመሮችን በተለያየ አቅጣጫ በማስመር ማቅለም





በተለያያ መንገድ የተሰመሩ መስመሮች




መስመሮችን በተለያየ አቅጣጫ በማስመር ቅርፅን መፍጠር

### 2.0.1. ማስመርን መለማመድ

**መልመጃ 5**

የሚከተለውን ቋሚ መስመር በደብተራችሁ ውስጥ በመደጋገም በማስመር ተለማመዱ፡፡



**መልመጃ 6**

የሚከተለውን አግድም መስመር በደብተራችሁ ውስጥ በመደጋገም በማስመር ተለማመዱ!



## መልመጃ 7

የሚከተለውን ሰያፍ መስመርን በደብተራችሁ ውስጥ በመደጋገም በማስመር ተለማመዱ!



## መልመጃ 8

የሚከተለውን ጠመዝማዛ መስመርን በደብተራችሁ ውስጥ በመደጋገም በማስመርተለማመዱ!



## መልመጃ 9

የሚከተለውን ዝግዛግ መስመርን በደብተራችሁ ውስጥ በመደጋገም በማስመር ተለማመዱ!



## መልመጃ 10

የሚከተለውን ሽክርክር መስመርን በደብተራችሁ ውስጥ በመደጋገም በማስመር ተለማመዱ!



## መልመጃ 11

የሚከተለውን ክብ መስመርን በደብተራችሁ ውስጥ በመደጋገም በማስመር ተለማመዱ!



## መልመጃ 12

የሚከተለውን ሞላላ መስመር በደብተራችሁ ውስጥ በመደጋገም በማስመር ተለማመዱ!



## መልመጃ 13

የሚከተለውን የደጋን መስመር በደብተራችሁ ውስጥ በመደጋገም በማስመር ተለማመዱ!

## መልመጃ 15

የሚከተሉትን ቅርፆች በደብተራችሁ ካነሳችሁ በኋላ ቀለም ቀቡ





## መልመጃ 16

**የሚከተሉትን ቅርፆች ከለያችሁ በኋላ ቀለም ቀቡ፡፡**





## 2.3. የቤተሰብ መዝሙር

**የግንዛቤ ጥያቄዎች**

የቤተሰብ መዝሙርን የሚዘምረው ማን ነው?
የቤተሰቦቻችሁ አባላት ሲዘምሩ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
የእያንዳንዳቸውን ድምፅ አስመስላችሁ ዘምሩ፡፡

### ለእናት መዝመር

ትግስተኛዋ እናቴ
ሁሌ አስብሳለሁ መዳኒቴ
ወልደሽ ያሳደግሽኝ እናቴ
መጥቼ እሰካይሽ ናፍቂያለሁ
እናቴ ከልቤ ወድሻለሁ
ኑሪልኝ ለዘላለም
እንዳንቺ ሚሆን ለኔ የለም/×2



## ተግባር

የእናት መዝሙርን ድምፃችሁን እንደ አባት እንደ እናትና እንደ ልጆች አስመስላችሁ በመዘመር ተጫወቱ፡፡

### ለአባት መዘመር

የኔ ትግስተኛ አባት
እኮራብሀለሁ በእውነት
አሳድገኸኛል ጥሩ ሰው አድርገህ
በጣም ቸኩያለሁ መጥቼ እስከማይህ
ኑርልኝ ለዘላለም
እንዳንተ ሚሆን ለኔ የለም/×2



### የነገሮችን ድምፅ በማስመሰል የመጫወት ተግባር

የአባት መዝሙርን ድምፃችሁን እንደ አባት እንደ እናትና እንደ ልጆች አስመስላችሁ በመዘመር ተጫወቱ!

# የእህትና ወንድም መዝሙር

**የግንዛቤ ጥያቄ**

1. ወንድምና እህት አላችሁ?
2. ትምህርት ቤት ለመምጣት ምን ዝግጅት ታደርጋላችሁ?
3. ወንድሜ የሚለውን መዝሙር ዘምራችሁ ታውቃላችሁ?





ወንድሜ ያእቆብ 2x
ተኛህ ወይ 2x
ደውል ተደወለ 2x
ተነሳ 2x
ላ ላ ላ....
እሺ እነሳለሁ 2x
እጄን ታጥቤ
ፊቴን ታጥቤ
ቁርሴን በልቼ
ወደ ትምህርት ቤት
እሄዳለሁ 2x

እህቴ ሜቲ 2x
ተኛሽ ወይ 2x
ደውል ተደወለ 2x
ተነሺ 2x
ላ ላ ላ...
እሺ እነሳለሁ 2x
እጄን ታጥቤ
ፊቴን ታጥቤ
ቁርሴን በልቼ
ወደ ትምህርት ቤት
እሄዳለሁ 2x



# የቤተሰብ መዝሙር



እናትና አባት
ወንድምና እህት
እነዚህ ባንድነት
የቤተሰብ አባላት/x 2

ወንድም እህት አሉኝ
ሁሌ የሚያግዙኝ
ጥሩ ልጅ እንድሆን
ሁሌ የሚመክሩኝ /

ሌሎችም ዘመዶች
ከኛ ጋር ሚኖሩ
እየተጋገዙ ስራም የሚሰሩ
እነርሱም እንዲሁ ቤተሰቤ ናቸው
ስለ ፍቅራቸው ክብር ሚገባቸው

## 2.4. መዝሙርና ውዝዋዜ/ጭፈራ በቀላል ምት

**የግንዛቤ ጥያቄዎች**

1. ጨፍራችሁ ታውቃላችሁ?
2. ምን ምን አይነት ጭፈራዎችን ታውቃላችሁ?

### ባህላዊ መዝሙር ከቀላል ጭፈራ ጋር

የሚከተለውን መዝሙር በቡድን ሆናችሁ ክብ በመስራት እያጨበጨባችሁና ከበሮ እየመታችሁ ተጫወቱ!



ጨረቃ ድንቡል ዱቃ

እጼ ቤት ገባች አውቃ

አፄ ቤት ያሉ ልጆች

ፈተጉ ፈታተጉዋት

በቁልፌት አስቀመጧት

ቁልፊቷ ስትሰበር
በዋንጫ ገለበጥዋት

አጃ ቆሎ ስንዴ ቆሎ
ይችን ትተሽ ያችን ቶሎ
ያችን ቶሎ /2

### ተግባር

ከምታውቁት የጭፍራ አይነቶች አንዱን መርጣችሁ ተራ በተራ በማጨብጨብ አሳዩ፡፡

## ማጠቃለያ

ህፃናት ባህላቸውን የሚያንፀባርቁ መዝሙሮችን በመዘመር ባህላቸውን እንዲወዱና እንዲያከብሩ ያደርጋቸዋል፡፡ እንዲሁም በቤተሰባቸው መካከል ፍቅርና መልካም ግንኙነት እንዲጠነክር ያደርጋል፡፡ /የመምህር መምሪያ ላይ ይሁን

# ምዕራፍ 3

## የታሪክና የባህል ተጨባጭ ሁኔታ

### 3.1. የአከባቢና የማህበረሰብ የስነ ጥበብ ስራዎች

**ተግባር**

በአካባቢያችሁ የእጅ ስራ ውጤቶችን አይታችሁ ታውቃላችሁ?

የአካባቢና የህብረተሰብ ስነ ጥበብ ሙያ የሚባለው ከጥንት ጀምሮ በህብረተሰቡ ውስጥ ሲሰራ የቆየ ሙያ ነው፡፡ ለምሳሌ ከሸክላ አፈር የሚሠሩ ጣባ ፣ ገበር ምጣድ፣ እንስራ፣ የመሳሰሉት ናቸው፡፡





## መልመጃ 1.

**በአካባቢያችሁ ከሸክላ የሚሰሩ ምግብ ለማበሰል የሚያገለግሉ እቃዎችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡**

ሌላው ህብረተሰብ ሞያ ሽመና ነው፡፡ ይህም ጥጥ በመፍተል የሚሰራ ሙያ ሲሆን ለምሳሌ ቡልኮ፣ ኩታ፣ጋቢ የተለያዩ ባህላዊ ልብሶች የመሳሰሉት ናቸው፡፡





የስፌት ስራ ሙያ የተለያዩ የስፌት ውጤቶች ለምሳሌ፡ ሰፌድ መሶብ ወንፊት እርቦ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡





የእንጨት ስራ ሙያ ከእንጨት የሚሰሩ እቃዎች ለምሳሌ አልጋ፣ የቤት በር፣ ጠረጴዛ፣ ወንበር እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡







የብረት ስራ ሙያ ከብረት የሚሰሩ እቃዎችን ያካትታል፡፡ ለምሳሌ መጥረቢያ፣ ቢላዋ፣ ማጭድ፣ ድጅኖ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡









የቆዳ ስራ ሙያ ከቆዳ የሚሰራ ሲሆን እንደ ጋሻ፣ ቁርበት፣ ስልቻ አንቀልባ እና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡



## 3.1.1. የባህል መዝሙር

አኩሪ ባህል አለን ለምሰሌ:

### የእንስሳት ሙገሳ መዝሙር



በጎቼና ላሜ እንደምን ዋላችሁ
በዱር ስትውሉ ምን ምን ገጠማችሁ
በቂ ምግብና ውሀ አገኛችሁ
ወይስ ሳትበሉ ያማችሁን ዋላችሁ፡፡





በሬዎቹ የታሉ ፍየሎቹም ጭምር
እንዴት እንደዋሉ እረኛው ይናገር፡፡
ግቡ በየተራ በየማደሪያችሁ
ተዘጋጅቶ ቀርቧል ይኸውአራታችሁ፡፡
ብሉ ጠጡ እረፉ በየ መኝታችሁ
መልካም ሌሊት ይሁን ሰላም ይብዛላችሁ/2

## የልጅነት መዝሙር

### የግንዛቤ ጥያቄ

- የልጅነት ጊዜ መዝሙር ዘምራችሁ ታውቃላችሁ?



እረ ልጆች ልጆች
እንጫወት በጣም
ከእንግዲህ ልጅነት
ተመልሶ አይመጣም
ልጅነቴ ልጅነቴ×2
ማርና ወተቴ

# የልጆች ጨዋታ

ይህን ጨዋታ ለመጫወት ጠያቂና መላሽ ያስፈልጋል፡፡ ጠያቂው በፍጥነት በመደጋገም ይጠይቃል መላሾችም በፍጥነት ይመልሳሉ፡፡ በዚህ መካከል የተሳሳተ መልስ የሚሰጥ ልጅ ይሳቅበታል፡፡

ለምሳሌ፡የሚከተለውን ተጫወቱ ከዱር እንስሳት ውጪ የመለሰ ልጅ ይሳቅበታል ማለት ነው፡፡

ጠያቂ፡ እንስሳት

መላሽ፡ የዱር እንስሳት

ጠያቂ፡ ምን ምን?

መላሽ፡ ጅብ



ጠያቂ: ምን ምን?

መላሽ፡ አንበሳ



ጠያቂ: ምን ምን?

መላሽ፡ ነብር



ጠያቂ፡ የሚበላ

መላሽ፡ ምግብ

ጠያቂ፡ ምን ምን?

መላሽ፡ እንጀራ



ጠያቂ፡ የሚጠጣ

መላሽ፡ ውሀ

ጠያቂ፡ ምን ምን?

መላሽ፡ ሻይ



## ልምምድ 7

1. በአካባቢያችሁ የምታውቁትን ማንኛውንም የልጆች ጨዋታ ተጫወቱ!

## 3.1.2. ተረት ተረት



የአሞራና የኤሊን ተረት ብዙ የዱር አራዊቶች በማሳተፍ ይነግሯችኋል፡፡ ሁለቱ ተራኪዎችና አንዳንድ እንስሳት ይህንን ተረት ይነግሩናል፡፡



## ሁለቱ ተራኪዎች







እርኩምና ኤሊ



ኤሊና ቁራ


ኤሊ ምን ሆነሻ?
በዱር ውስጥ ብዙ ጓደኞች አሉሽ
ሰውነትሽ በድንጋይ ተሸፍኗል ጉዳት ሊደርስብሽ ኣይችልም
እኔ በአየር ላይ መብረር እፈልጋለሁ
እና ሁለታችን መብረር አንችልም ።የማንችለውንም አንመኝም

ኤሊ በረጅሙ ተንፍሶ እንዲህ አለ





በዱር መኖር በጣም ሰልችቶኛል
ስለዚህ ወፍ ወደ ሰማይ
እንድትወስደኝ መጠየቅ አለብኝ

( በዚህ ጊዜ ወፍ እንዳጋጣሚ ወደ እነሱ መጣች) ኤሊም ወፍን አይታ ተደነቀች





ወፍቱ የሰማይንና የምድርን
ድንቅ ነገሮች እንዳይ ወደ ሰማይ
ውሰጅኝ አለቻት

ተይ በዚህ አይነት ነገር ላይ ላግዛሽ
አልችልም



በዚህ መካከል እርኩም መጣ





እርኩም እባክህ ወደሰማይ እንድበር አግዘኝ



እርኩም አይ አንቺ በጣም ስለምትከብጂ
ላግዝሽ አልችልም ብሏት ሄደ

በመቀጠል እርግብ መጣች





እርግብ በሰማይ ላይ እንድበር አግዢኝ

ተይ አንቺ ክንፍ የለሽም ለመብረርም አልተፈጠርሽም



ብላ ትታት ሄደች በዚህ ጊዜ ቁራ መጣ



## 3.1.3. እንቆቅልሽ




1. አፍዋን ከፍታ ሰውን የምታይ= እንስራ



2. ጠዋት አይቻት ማታ አጣኋት= ጤዛ



3. መሬት ትሮጣለች ውሻ ትመስላለች= ቀበሮ



4. ህይወት ያለው ሙት የሚሸከም
ሙት ህይወት ያለውን የሚሸከም=
ፈረስና ኮርቻ



5. ሲበላ ይድናል ሲጠጣ ይሞታል= እሳት



6. አይን ያለው አጥንት የሌለው = እንጀራ



መልመጃ 1

1. በአካባቢያችሁ የሚታወቁ እንቆቅልሾችን ከጓደኖቻችሁ ጋር ተጫወቱ!

## 3.2. የአካባቢ ቀለማት

የአካባቢ ቀለማት ማለት በአካባቢ የሚገኙ የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ቀለማት ማለት ነው፡፡ በአካባቢያችን የሚገኙ የተፈጥሮ ቀለማት ውስጥ ጥቂቶቹ የእጽዋት ቀለም፣ የቤት እስሳት፣ የዱር አራዊት፣ የወፎች፣ የአፈር አይነቶች፣ የሰው ሰራሽ ቁሳቁሶች ቀለማት እንደ ልብስ፣ መኪና ፣ቤትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

### 3.2.1. የተለያዩ አበቦች ቀለማት







## መልመጃ 3

**የሚከተሉትን ስእሎች ከነደፋችሁ በኋላ የተቀቡትን እያያችሁ አመሳስላችሁ ቀቡ!**



## 3.2.4. የአባ ገዳ እና የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባንዲራ ቀለማት



የአባገዳ ባንዲራ



የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባንዲራ

### መልመጃ 4

**ከዚህ በታች የተሰጡትን ስእሎች ነድፋችሁ የምትፈልጉትን ቀለም ቀቡ!**



# ምእራፍ 4

# የስነ-ጥበባት ማራኪነት

## 4. አስደናቂ የባህል ክንውን

### 4.1. የቤተሰብ መዝሙርና ውዝዋዜ

**ተግባር 1**

1. እስከ አሁን ከተማራችኋቸው መዝሙሮች ውስጥ ምን ምን ታስታውሳላችሁ?
2. ከመዝሙሮቹ አንዱን በክፍል ውስጥ ዘምሩ፡፡

**ተግባር 2**

እስካሁን የተማራችሁትን መዝሙር ከውዝዋዜ ጋር ማሳየት ትችላላችሁ? ሁለት ምረጡና ከተለማመዳችሁ በኋላ ለክፍል ተማሪዎች አሳዩ!



## ተግባር 3

ከምታውቁት መዝሙር ውስጥ በይበልጥ የምታደንቁትን ለጓደኞችሁ ንገሩ!



## አንድ መዝሙር አድናቆት እንዲያገኝ:-

1. መወደድ አለበት፡፡
2. ጥሩ መልክት ማስተላለፍ አለበት፡፡
3. ለሰው የሚመች እና
4. የማይዘነጋ መሆን ይኖርበታል፡፡

## 4.2. የቤተሰብን የስራ ድርሻ በድራማ መልክ መግለጽ

### 4.2.1 ቤተሰብ በእሬቻ በአል ላይ ያላቸውን ድርሻ አስመስሎ መጫወት

የዚህ ትምህርት ዋና ትኩረት የባህል ክንውኖችን ማድነቅ በመሆኑ የቤተሰብን ድርሻ አስመስሎ መጫወት ስለ ባህላችሁ እንድትማሩ የሚያግዛችሁ ነው፡፡ እናንተም በእሬቻ በአል ላይ ቤተሰቦቻችሁ የሚከውኑትን ክዋኔ አስመስላችሁ ተጫወቱ!



ህፃናት ጠዋት ከእንቅልፋቸው ተነስተው አይናቸውን እያሻሹ ወደ ውጪ ሲወጡ እናትና አባታቸው በባህል ልብስ አጊጠው ሳር በእጃቸው ይዘው ያያሉ::








ወንዶችና ሴቶች ጎረቤቶቻቸው ይመጣሉ::



ልጅትዋ ከምትናገረው መጨረሻው ያላ አግባብ የገባ ነው ይውጣ እንዲሁም መጀመሪ ላይ ያለው የህፃናቱ ስእል ከእንቅልፍ ገና የተነሱ ልጆች አይምስልም ቢያንስ በለሊት ልብስ ቢሆኑ የበለጠ ጥሩ ይሆናል



## የእሬቻ መዝሙር

### ተግባር

የእሬቻ መዝሙር መምህራችሁ ሲያለማምዷችሁ ትኩረት በመስጠት ተለማመዱ፡፡ ከዚያም ከቡድናችሁ አባላት አንዱ አንደ መሪ ሌሎቻችሁ ተቀባይ ሆናችሁ ከውኑት፡፡

### መልመጃ

1. በአካባቢያችሁ የሚደረግ አንድ የባህል ክንውን አስመስላችሁ ተጫወቱ!

# ፬.3 የቤተሰብ ስዕል

## 4.3.1 የቤተሰብ አባላት በስዕል



የቤተሰብ አበላት ባንድነት ምግብ ሲመገቡ



የቤተሰብ አባላት የቤት ውስጥ ስራዎችን ሲተጋገዙ



የቤተሰብ አባላት  የተለያዩ ስራዎችን ሲሰሩ የሚያሰይ ስዕል



የቤተሰብ አበላት በዓል ለማክበር የባህል ልብስ ለብሰው



ቤተሰብ እሬቻ በአል ለማክበር ሲሄዱ



አዛውንት እንጨት ስር ተቀምጠው ልጆችን ተረት ተረት ሲያስተምሩ



ቤተሰብ ለልጆቻቸው ታሪክ ሲነግሩ

# ምእራፍ 5
# የስነጥበባት ግንኙነት

## 5.1. በቡድን በመዘመር የራስን ተፈጥሯዊ ድምፅ ማሳደግ

### 5.1.1. የሀገር መዝሙር

**የግንዛቤ ጥያቄ**

የሀገር መዝሙር ታውቃላችሁ? መምህራችሁ የሚያዘምሯችሁን መዝሙር ዘምሩ።



## 5.1.2 የቁጥርና የወራት መዝሙር

**የግንዛቤ ጥያቄ**

1. የቁጥርና የወራት መዝሙሮች ሲዘመሩ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
2. ቁጥሮችን መቁጠር ትችላላችሁ?




30...40....50...60...70...80...90...100.

3. የአመቱን ወራት መናገር ትችላላችሁ?

መስከረም፣ ጥቅምት፣ ህዳር፣ ታህሳስ፣ ...... ብለን እንነሳለን

**ተግባር**

መምህራችሁ አረንጓዴ ጠርሙሶች የሚለውን መዝሙር ሲዘምሩላችሁ እየተከተላችሁ ተለማመዱ፡፡ ከዚያም በቡድን በአንድነት ዘምሩ፡፡

# አረንጓዴ ጠርሙሶች መዝሙር

| | |
|---|---|
| አስር | አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ |
| ድንገት | አንዱ ወድቆ ቢሰበር ዘጠኝ ይቀራል፤ |
| ዘጠኝ | አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ |
| ድንገት | አንዱ ወድቆ ቢሰበር ስምንት ይቀራል፤ |
| ስምንት | አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ |
| ድንገት | አንዱ ወድቆ ቢሰበር ሰባት ይቀራል፤ |
| ሰባት | አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ |
| ድንገት | አንዱ ወድቆ ቢሰበር ስድስት ይቀራል፤ |
| ስድስት | አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ |
| ድንገት | አንዱ ወድቆ ቢሰበር አምስት ይቀራል፤ |
| አምስት | አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ |
| ድንገት | አንዱ ወድቆ ቢሰበር አራት ይቀራል፤ |
| አራት | አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ |
| ድንገት | አንዱ ወድቆ ቢሰበር ሶስት ይቀራል፤ |
| ሶስት | አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ |
| ድንገት | አንዱ ወድቆ ቢሰበር ሁለት ይቀራል፤ |
| ሁለት | አረንጓዴ ጠርሙሶች በግድግዳ ላይ |
| ድንገት | አንዱ ወድቆ ቢሰበር አንድ ይቀራል።×2 |

## 5.1.3. የሚያማምሩ ኳሶች መዝሙር





### የሚያማምሩ ኳሶች መዝሙር

የሚያማምሩ ዘጠን ኳሶች አሉኝ
አንዱን ስለጋ ስምንት ቀሩኝ
የሚያማምሩ ስምንት ኳሶች አሉኝ
አንዱን ስለጋ ሰባት ቀሩኝ
የሚያማምሩ ሰባት ኳሶች አሉኝ
አንዱን ስለጋ ስድስት ቀሩኝ
የሚያማምሩ ስድስት ኳሶች አሉኝ
አንዱን ስለጋ አምስት ቀሩኝ
የሚያማምሩ አምስት ኳሶች አሉኝ
አንዱን ስለጋ አራት ቀሩኝ
የሚያማምሩ አራት ኳሶች አሉኝ

አንዱን ስለጋ ሶስት ቀሩኝ
የሚያማምሩ ሶስት ኳሶች አሉኝ
አንዱን ስለጋ ሁለት ቀሩኝ
የሚያማምሩ ሁለት ኳሶች አሉኝ
አንዱን ስለጋ አንድ ቀረኝ
አንድ ኳስ አለችኝ የታምር በጣም
በደንብ ይዛታለሁ እሷስ ከጄ አትወጣም ፡፡/×2



## 5.1.4. የቤት እንስሳት መዝሙር



የቤት እንስሳት ይዘምራሉ
ድምፃቸውን ያሰማሉ 2×

ድመት ትዘምራለች
ሚያዉ ሚያዉ ትላለች
ወተት ትጎነጫለች



የቤት እንስሳት ይዘምራሉ
ድምፃቸውን ያሰማሉ 2x
ውሻም ትጮሀለች
ውው ውው ትላለች
አጥንት ትቆረጥማለች

## 5.1.5. የንፅህና አጠባበቅ መዝሙር



ዘወትር ጠዋት ተነስተን
መፀዳጃ ቤት እንሄዳለን

እጃችንን ፊታችንን
ታጥበን በሳሙና
ጥርሳችንን ደግሞ እናፀዳና
ቁርሳችንን እንበላለን
ፈጣሪያችንን አመስግነን 2x
ከዚያም አንግተን ቦርሳችንን
ትምህርት ቤት እንሄዳለን
ይህን ሁሌ እንከውናለን 2x

## 5.2. የታሪካዊ ቦታዎች ግንኙነትና ትግበራ

### የቡድን ገፀባህሪን ወክሎ መጫወት



በዚህ ምእራፍ ውስጥ ከዚህ በፊት እንደተማራችሁት የትወና ድርሻችሁ እንደሚከተለው ቀርቦላችኋል፡፡ በዚህ ፅሁፍ ላይ ተመስርታችሁ ሰፊ ጊዜ በመውሰድ ተለማመዱ!

ለምሳሌ፡ የአስተማሪን ድርሻ ወስዶ የሚጫወተው/የምትጫወተው እንደ መምህር በመልበስ፣ መነፅር በማድረግ፣ ጠመኔ፣ ዳስተር እና ፊሽካ በመያዝ ተማሪዎች ወደ ክፍል እንዲገቡ በመጥራት ይጀምር/ትጀምር



መምህር: (ፊሽካ በመንፋት) ወደ ክፍል ይግቡ

ተማሪዎች ክፍል ከገቡ በኂላ



መምህር/ት: ሴንጮ ደብተርህን ለምን አታወጣም?



ሴንጮ: እቤት ነው ያለው

ሁሉም የክፍል ተማሪዎች ይስቃሉ



**መምህር/ት:** ትናንት ስለ ኦሮሚያ ታሪካዊ ቦታዎች ተምረናል.
እስቲ ዛሬ መልሰን እናስታውስ?
እኔ እጀምርላችኋለሁ! እናንተ ደግሞ ለቡድናችሁ ንገሩ




**መምህር/ት:** ኦሮሚያን እንዞራለን 2x

**ቡድን 1: ታሪካዊ ቦታዎችን እንጎበኛለን**

**መምህር/ት:** ከወሊጋ እንጀምራለን

**ቡድን 2: የኩምሳ ሞሮዳን ቤተመንግስት እንጎበኛለን**



**መምህር/ት:** በዚያው ጂማ እንሄድና

**ቡድን 1: የአባጅፋርን ቤተ መንግስት እንጎበኛለን**



መምህር/ት: ወደ አርሲ ሄደን አኖሌ እናያለን

ቡድን 2: የአኖሌ ሀውልትን እናያለን



መምህር/ት: ባሌ ባልዩ እንሄዳለን

ቡድን 1፡ ድሬ ሼከ ሁሴንን እንጎበኛለን



**መምህር/ት:** ሀረርጌ የፍቅር አገር እንሄዳለን

**ሁሉም ተማሪዎች: የጨለንቆን ሀውልት እንጎበኛለን**



ወደ ሐረር ሄደን ጀጎል እንጎበኛለን

**ሁሉም ተማሪዎች: ጀጎል ግንብን እንዞራለን**



# 5.3. የታሪካዊ ቦታዎች በስዕል



የኩምሳ ሞሮዳ ቤተ መንግስት



የአባ ጅፋር ቤተ--መንግስት



ድሬ ሼክሁሴን




የጀጎል ግንብ



የጨለንቆ ሀውልት



የአኖሌ ሀውልት



የአባ ሙዳ አዳራሽ

ለግራፊክስ በየምእራፉ ያሉ ስእሎች መጠን ተመጣጣኝ አይደለም አንዱ ትልቅ አንዱ በጣም ትንሽ ነው ይህ ደሞ መፅሀፉ ውበት እንዳይኖረው ስለሚያደርግ በተቻለ መጠን ተመጣጣኝ ቢሆኑ።